# አቅጣጫችን ይቀየር

## ከዓሣዬ

ሃገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ.........እየተባለ ሃገርን የከዳ፣የገደለና የበደለን የመሾምና የመሸለም ጎጂ ባሕላችን መሥመር ተሰምሮበት፣አዲሥ አቅጣጫን በመቀየሥ ለሃገር የታገሉትንና፣የተዋደቁትን፣አሁንም እየታገሉና እየተዋደቁ ያሉትን እውቅና ሰጥቶ፣የማክበርና የመዘከር አቅጣጫን መያዝ ይኖርብናል እላለሁ ። ከትላንት ወድያና ትላንት የሃገር ጠላት ሁነው፣ከፋሺስትና ከዘረኛው ጋር ወግነው በጭካኔ በገደሉትና ባፈሰሱት የጀግኖች ደም ላይ ቆመው አሁንም በየመሥኮቱ የቅርሻት ዛራቸውን ሲያጓሩ ዝም ብሎ ማዳመጥና ማዳነቅ ያሟል ። ሃገርንም ይጎዳል ። ይኸንን በሂደት እየቀጠለ ያለውን ገዳይን የመጥቀምና የመደገፍ ጎጂ አቅዋምን ለመቀየር ወቅቱ ትላንት ካልነበረ ዛሬውኑ መጀመር አለበት እላለሁ ።

በጫካና በሥልጣን ላይ ሁነው ሃገርን ሲገነጥሉና፣ ሲመዘብሩ፣በሃይማኖት ተቋማት ላይ ሣይቀር በአንዋር መስጊድና፣በአደባባይ እየሱስ ምዕመናንን ሲያስጨፈጭፉ የነበሩ፣ አማራ ነህ እያሉ በገደል ሲያስወረውሩ የነበሩ ፣ ሰቆቃና ፍጅትን ያፋፋሙና የፈጸሙ፣ አፍነውና ማርከው የወሰዱትን መዳረሻ ያሳጡና ለፍርድ ሣያቀርቡ፣ ከሰባአዊነት ውጭ በሆነ መንገድ በየጉድጓዱ ውሥጥ አሥረው እያሰቃዩ የነበሩትን ፣ አሁን ግን በሥልጣንና በጥቅም ብቻ ተጣልተው ሥለተለያዩና ያው በለመዱበት በዘረኝነት ቦያቸው ፈሥሰው <u>አረና</u> ብለው ልንመራችሁ መጣን ሲሉ አጨብጭቦ መቀበል ወንጀል ነው ። ሃገርንና ሕዝብን ለቀጣይ እርድ ማዘጋጀትም ሥለሆነ ማውገዝ እንጂ፣ለፍርድ ማቅረብ እንጂ፣ወንጀላቸውን ሣይናዘዙና ይቅርታን ሣይጠይቁ እንኳንስ መሪ አድርገን ልንቀበላቸው ቀርቶ ወደ ሕዝብ ጎራም እንዲቀላቀሉ መፍቀድ ተገቢ አካሄድ አይደለም እላለሁ ። እዚህ ላይ ነው ወንጀለኛን የመሾምና የመሸለም አሮጌው አቅጣጫ ተወግዞና ተሰምሮበት በአዲሥ አቅጣጫ ሰውን በሙያውና በተግባሩ እየለኩና እየመዘኑ ለሃገር ለሕዝብና ለትግሉ ውጤትን ሊያስመዘግቡ የሚችሉትን በትግል የተፈተኑትን ብቻ መቀበልና ማሥቀመጥ የሚገባን የምለው ።

አንድ የፖለቲካ ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራሙን በመንደፍ በሕዝብ ውሥጥ ምልመላና ቅሥቀሣን እያካሄደ አባላቱን በማብዛት በሚያደርገው እንቅሥቃሴ እውቅናንና ተሰሚነትን ያገኛል ። በትግሉ ሂደት ላይም አሻራውን ያሣርፍበታል ። ታድያ ዛሬ ሥማቸውና ህልውናቸው በሕዝብ ሣይታወቅ ሥልሣና ሰባ ድርጅቶች ለምርጫ ቀረቡ የሚባል የቀልድ ቧልት የሚካሄደው በኛይቱ ጉደኛ አገር ብቻ ነው ። የሰላማዊ ትግል አባወራ ነን እያሉ የሕዝብ ጥያቄ የማይነሳበትና ለተለጣፊነት የወንበር ምርጫ ሲሉ ለዘረኛውና ለአምባገነኑ አገዛዝ በአሥር ጣታቸው ፈርመው ሽፋንና እውቅናን እየሰጡ ከኛ በላይ ታጋይ ለአሣር በማለት በሕዝብ ሰቆቃ ላይ በመሾምና በመሸለም ከሕዝብ ጠላት ጋር ጽዋን እያጋጩ መመጻደቅ የሚቻለው አሁንም በዚህቹ አሣዛኝዋ አገራችን ውሥጥ ነው ። እንደገናም ሶሥትና አራት አባል ያላቸው እራሣቸውን እንደ ድርጅት ቆጥረው ሕብረት ሕብረት ብለው ሲጮሁና ፣እሺ ለሕብረቱ የምታቀርቡት የሰውና የገንዘብ ሃይል አላችሁ ወይ ተብለው ሲጠየቁ ዓይናቸው የሚፈጠው፣ ወይም ደግሞ ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚሉትን፣በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ጠላታችን አይደለም የሚሉትን ሁሉ ሕብረት ካላችሁ ኢትዮጵያዊነትንና ትግሉ የሚጠይቀውን መሥፈርቶች አሟልታችሁ ከተገኛችሁ ብቻ ነው በሕብረት አብረን ልንሰራ የምንችለው ብሎ ኢሕአፓ እቅጩን ሥለነገራቸው፣እንደ ጸረ ሕብረት ተቆጥሮ የሚወገዘውና ቡራ ከረዩ የሚጨፈርበት አሁንም በኛይቱ ጉደኛዋ አገር ተቃዋሚ ተብየዎች ብቻ ነው ። ሥለዚህ ይህ ሃቁን የሣተ አቅጣጫ ተቀይሮ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንከተል የምለውም ከዚህ አንጻር ነው ።

ሕዝቡ ያልመከረበትንና ያልተቀበለውን የደደቢትን ውል ሕግ ብለው በመቀበል ምርጫ በሚል ቧልት ፈርመው የተወዳደሩትን ተቃዋሚዎች በዝርር አሽነፍኳቸው፣ከእንግዲህ ንጉሡ እኔ ነኝ ባለ ማግሥትና፣ሕዝቡም ተቃዋሚ ነን በሚሉት ላይ ተሥፋ ቆርጦ በነበረ ግዜ፣ፍቃድ ሣይጠይቅ፣ሥነ ምግባር ሣይፈርም አፈዳቪት ሣይሞላ በሃገሬ ላይ ማናባቱ አዛዥና ናዛዥ አለብኝና ብሎ በመናገሻ ከተማው ለማይቀረው ፍልሚያ ተጠንቀቃችሁ ጠብቁኝ  ከጎናችሁ ነኝ! የሚለውን ወረቀቱን ሲበትንና ለሕዝቡ ተሥፋ ሆኖ፣ግን የወያኔን ዓይን ሲያስፈጥጥ፣ የዚያን ግዜ የትግሉ ሥልትና አቅጣጫ ተቀይሮ የመድረኩ ተዋናዮች ኢሕአፓና ሕዝቡ በአንድ በኩልና ፣ ወያኔና ደጋፊዎቹ ደግሞ በሌላ በኩል መሆናቸው ተረጋገጠ ። እዚህ ላይ ነው የትግሉ አቅጣጫ እንዴትና በእነማን እየተመራ እንደሆነ

ለወዳጅም ለጠላትም ግልጽ ሆኖ የወጣው ። ሥለዚህ ይህንን ተጨባጭ እውነታ መሰረት አድርገን ትክክለኛውን አቅጣጫ በመያዝና በመከተል ሃገራችንን ከውድቀቷ ለማዳን ሃይላችንን አሰባስበን የዜግነት ግዳጃችንን ለመወጣት አቅም ችሎታና ብቃት ያለውን ድርጅት በመርዳትና በመደገፍ ትግላችንን ይበልጥ ማቀጣጠልና ማፋፋም አለብን የምለውም ከዚህ ተጨባጭ ሃቅ በመነሣት ነው ።

ወያኔ በብቸኝነትና በአምባገነንነት በተቆጣጠራት ኢትዮጵያ ውሥጥ ዛሬም የዩዲጄ፣የመኢአድ፣የመድረክ፣ ወ.ዘ.ተ. አባል ነኝ ሥላሉ የሚወሰድባቸው አንድም እርምጃ የለም፣ግን በሌላ በኩል ደግሞ የኢሕአፓ አባል ወይም ደጋፊ ነኝ ማለት ቀርቶ የኢሕአፓን ሥም ማንሣት ብቻ በግዞት፣በእሥራትና በሞት ያሥቀጣል ። ይህ ሁኔታ ታድያ እውን ወያኔ ኢሕአፓ በአገር ውሥጥ ሥለሌለ በንቀት ዓይን ተመልክቶት ነው የሚለውን የወያኔን ውሸትና የምኞት አነጋገር አጠያያቂ አያደርገውም ብላችሁ ታሥባላችሁ? እንደገና ደግሞ ግንቦት 7 በሻቢያ እየተረዳ መንግሥቱን በሃይል ሊያስገለብጥ የላካቸውን ጸረ መንግሥት ሃይሎች ያዝኳቸው ያለው ወያኔ፣አሁንም በሻቢያ የተላኩ የኦሮሞ ነጻ አውጪዎችንና፣የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ሃይል አባሎችን ያዝኩና ደመሰሥኳቸው ብሎ በራድዮና በቴሌቪዥን የለፈለፈው ወያኔ፣ኢሕአፓ በመናገሻ ከተማው ሕዝቡን ለማይቀረው ፍልሚያ ተዘጋጁና ጠብቁ ከጎናችሁ ነኝ ብሎ ሙሉ በሙሉ በወያኔ የጸጥታ ቁጥጥር ሥር ወድቃ በምትገኘው የአዲስ አበባ ከተማ ከዳር እሥከ ዳር የቅስቀሣ ወረቀቶቹን ሲበትንና የዓለም ጋዜጠኞች ሲዘግቡት፣እሱ ግን ትንፍሽ ያለማለቱ እውን ወያኔ ኢሕአፓን ንቆት ነው ያሰኛል? በሌሎች ድርጅቶች ሣይሆን በኢሕአፓ ላይ ብቻ የወያኔ የኢሕአፓ የሥለላ ዴሥክ ተቁቁሞ ኢሕአፓ፣ኢሕአፓ የሚሸቱትን እየሰለለ በተገኙበት ቦታ ፍርድ ቤት ሣያያቸው እንዲታሰሩና እንዲገደሉ ያደረገውና እያደረገም ያለው እውነት ተሰደዋል ጠፍተዋል ብሎ ሥለናቃቸው ይመሥላችኋል?እዚህ ላይ ነው በአስተሣሰብም በአመለካከትም፣አሉባልታውን ትተን የውሸት ጥሩንባውን አሥቁመን ሃቁንና ዕውነታውን ለይተን መጨበጥ አለብን የምለው ።

ሃቁና እውነቱ ግን ዘረኛው ወያኔ ተንኮታኩቶ የሚወድቀው ኢሕአፓ በሚመራው የህዝብ አመጽ ብቻ እንደሆነ ሌላ ሣይሆን ወያኔ እራሱ ጥርት አድርጎ ያውቀዋል ። ኢሕአፓና ሕዝቡ ዓሣና ባህር መሆናቸውንም ጠንቅቆ ሥለሚረዳ መጣባችሁ ብሎ እንደ ሌሎቹ ድርጅቶች በኢሕአፓ ላይ የቅስቀሣ ዘመቻ ሊያካሄድ ፈጽሞ አይችልም ። ቢሞክርም፣እሱ ከመጣልንማ ብሎ የሕዝቡ አመጽ ከዳር እስከ ዳር እንደሚፈነዳበት ይገነዘባልና ። ይህ የአመጽ እንቅሥቃሴም በሂደት ያለ ሥለሆነ በመላ አገራችን መፈንዳቱ የማይቀር የጊዜ ጉዳይ ነው ። የትግሉ አቅጣጫም ተቀይሶ ገሃድ ሆኗል ። ኢሕአፓ የሥደተኛ ድርጅት ሆኖ የሚገኘውም በወያኔ የምኞትና የውሸት ፋብሪካ ውሥጥ ብቻ ነው ። ሥለዚህ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ የምንገኘው ኢትዮጵያውያን አገር ወዳድ በሙሉ ትክክለኛውን አቅጣጫ ተከትለን የኢሕአፓን የትግል ጥሪ ተቀብለን ሃገርን ለማዳን ወቅቱ ለሚጠይቀን የዜግነት ግዳጅ መልሥ ለመሥጠት ቀነ ቀጠሮ ሣንጠይቅ አሁኑኑ እንነሣ እላለሁ ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ሞት ለወያኔ !
12/11/10

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.